ለመሆኑ የስድ ገበያ ኢኮኖሚ የማን ምርጫ ነው?

በዚህ ዝግጅታችን ከአደይ አበባ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ ሁለት መቶ ያህል ሠራተኞች ከሥራ መባረራቸው ተነግሯል። ባለፉት ዓመታት በዚህ መልክ በደርዘን ሺ የሚቆጠሩ ወዛደሮችና የመንግሥት ሠራተኞች ከሥራ ተፈናቅለው ድሮም ቢሆን ካልተሟላ ኑሮአቸው ወደ ባሰ ሲኦል ወርደዋል። ገበሬዎች ከሚያርሱት መሬት ተፈናቅለው ለጅብ ተዳርገዋል።

ድሃ ነጋዴዎች መተዳደሪያቸውን ተቀምተው ጉሮሩቸው ተዘግቷል። በዚያም ልክ ደግሞ ጥቂቶች በግርግር በማካበት ላይ ባሉት መጠን የለሽ ሃብት የተነሳ ሃገራችን በታሪኪ አይታውና ሰምታው በማታውቀው ሁኔታ የገቢና የኑሮ ደረጃ መበላለጥ ሰማይ እየነካ ሲሄድ እናያለን። በዚህ መልክ በየእለቱ ቁጥራቸው እየጨመረ የሚሄድ ኢትዮጵያውያን በየእለቱ ከፋቱ እየጨመረ ለሚሄድ ድህነት መታረዝና ውርደት እየተዳረጉ የሚሄዱበት አስከፊ ሥርዓት ውስጥ ገብተዋል።

የዚህ አስፈ ሂደት መሠረታዊ ምንጩ በህዝብ ፊት ምንም ተጠያቂነት የሌለው ጥቂቶች ለጥቂቶች ያቋቋሙት ጸረ ህዝብ መንግሥት መኖሩ ነው። ይህ በሃገራችን የተለመደ የአገዛዝ ሥርዓት ነውና ምንም አዲስ ነገር የለውም ይባል ይሆናል። አለው። በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ በዚህ ህዝባችን ትከሻ ላይ ከቆየው የጭቆና አገዛዝ ቀንበር ላይ ሌላም ቀንበር ተጭኖበታል። ይኸውም በኢፍትሃዊነቱ ራሳቸው ተጠቃሚዎቹ አንዳንዴ ሊኮንኑት የሚቃጣቸው ቅጥ ያጣ የነጻ ገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት ነው። እንዲህ ዓይነቱ የኢኮኖሚ ሥርዓት በርግጥም በፖለቲካው መስክ ዲሞክራሲን የሚያራምድ አገዛዝ ባለባቸው አካባቢዎች አንዳንድ መጠን የሳቱ ግፎቹ እየታረቁ ለአንድ አገር እድገትን ሊያመጣ ይችላል። ህዝብ ሲበደል ተቃውሞ ለማሰማት በማይቸልባቸው፣ የመንግሥት ፖሊሲ አልመች ሲለው ያንን መንግሥት ለመለወጥ በማይቸልባቸው፣ ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች እንደልብ እየተረጡ፤ አለ የሚባለው መንግሥት ህዝቡን በጭቆናና በማሸበር ብቻ በሚገዛበት አገር ከነጻ ገበያነቱ ስድ ገበያነቱ የሚያመዝን ከግፈኛም ግፈኛ ሥርዓት ሊሆን ይችላል። ዛሬ ወያኔና ግብረ አበሮቹ በህዝባችን ላይ በመትከል ላይ ያሉት ሥርዓት እንዲህ ዓይነቱ የስድ ገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት ነው። ይህ ሥርዓት በሃገራችን እንዲያንሰራራ ሁለት ሰበቦች ይሰነዘራሉ።

1ኛ/ ይህንን ሥርዓት የራሱ የኢትዮጵያ ህዝብ ምርጫ አስመስሎ ለማቅረብ የሚደረገው ሙከራ አለ። ከአንድ ዓመት በፊት የዚህ የስዱ ገበያ ግርግር ቀንደኛ ተጠቃሚ ከሆኑት ዜጎች አንዱ አቶ መለስ ዜናዊ በሰጡት ጋዜጣዊ ጉባኤ ላይ ስለዚህ ጉዳይ አንስተው ሲተቹ ‘የነጻ ገበያ ሥርዓት መርጠናል። እርግጥ ይህ ሥርዓት አንዳንድ ጉድለቶች አሉት። ግን አንዴ ተመርጧልና ልጅን ሲወዱ ከነንፈጡ ነው በተባለው መሠረት…’ ሥርዓቱን ከነግፈኛነቱ መቀበል እንደሚስፈልግ ተናግረዋል። ተልካሻ ሰበብ ነው። የቀበሌ ዳኛ ሆነ የወረዳ አስተዳዳሪውን በመሰለው መንገድ አትመርጥም ተብሎ በመንደሩ ጣፊያ የተነፈገ ዜጋ በአገር ደረጃ የሚስማማኝን ዲሞክራሲ ስደዱልኝ ብሎ በጠየቀው መሠረት ይህ ሥርዓት ተገንብቶለታል ቢሉን አቶ መለስን ከራስዎ በስተቀር ማንንም አያታልሉም እንላቸዋለን። የኢትዮጵያ ህዝብ ይህንን የነጻ ገበያ ሥርዓት ፈልጎ ይምረጠ አይምረጥ ሌላ ራሱን ይቻል ጥያቄ ነው። እዚህ ላይ ማለት የምንፈለገው ህዝቡ መርጦ ነው የሚለው አነጋገር በሬ ወለደ አነጋገር ነው ለማለት ብቻ ነው።

2ኛ/ ይህ ሥርዓት በሃገራችን በመተከል ላይ ያለው በዓለም አቀፉ ሁኔታ ግፊት ነው የሚል ክርክርም አለ። በእርግጥም ምንም እንኳን ከእለት እለት እየሰፋና እየተቀናጀ የሚሄድ ተቃውሞ እያጋጠመው ቢሆንም ይህ ሥርዓት በአንድ ወጠንት በድፍን ዓለም ለማንሰራራት እየሞከረ መሆኑ አይካድም። ግን ይህም ሆኖ በህዝብ ፊት ተጠያቂነት ያላቸው፣ ሃገርና ህዝብን የሚያፈቅሩ፣ ከስግብግብነትና ከግል ጥቅም ትንሽ እልፍ ያለ ራእይ ያላቸው መሪዎች በታደሉ አገሮች የዚህን ዓለም አቀፋዊ ጫና አስከፊ ውጤቶች ለመቋቋም፣ ዜጎችን ለጅብ ላለመዳረግ የተሳኩ ሲካሄድ እናያለን። በዚህም የተነሳ የኢትዮጵያ ገዥዎች የነሱን ግፍ በዓለም አቀፋዊ ጫና ሲለጥፉ ማንም አያምናቸውም።

ባጭሩ ዛሬ ባለው ሁኔታ ይህ ስድ ሥርዓት የኢትዮጵያ ህዝብ ምርጫ አይደለም ዓለም አቀፋዊ ግፊት የተባለውም ሰበብ ሆኖ ሊቀርብ አይችልም። የኛ ዋናው ችግር ዲሞክራሲያዊና ለህዝብ የቆመ አስተዳደር ማጣት ነው። ዛሬ በዚህ ሥርዓት ሳቢያ ለከፋ ችጋር በመጋለጥ ላይ ያሉት በሚልዬን የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ለተደላደለ ኑሮ ማድረግ የሚገባቸውን ትግል ያላፋፋሙት እነዚህን ሰበቦች አምነው በመቀበል ወይም ደግሞ የበየ ተመልካችነት ኑሮ ስለተስማማቸው አይደለም። ለህልውናቸው የሚያደርጉትን ትግል አቅጣጫ እያሳየ፣ የሚመራ፣ ወግ ላለው ኑሮ ያላቸውን ህልም የተቀነባበረና ተአማኒነትም ያለው አማራጭ አድርጎ የሚያቀርብላቸው የፖለቲካ አመራር ባለመታደላቸው ነው።

የወያኔ አክራሪዎች ብሄርን ከብሄር፣ ህዝብን ከህዝብ እያጋጩ በፈጠሩት የገበያ ግርግር እየተጠቀሙ እነሱም ሆኑ የሌሎች ብሄሮች ግብረ አበሮቻቸው በሚልዬንኖች እንባ ላይ የደስታና የፍስሃ ደሴቶች ሲገነቡ ድፍን አገር አንዳንድ መሰረታዊ ሃቆችን ረስቶ በነሱ ወጥመድ የተያዘ ይመስላል። መሠረታዊው ሃቅ ግን አንድ ነው። ዛሬ ከአደይ አበባ የተባረሩትም ሆነ የቀደሟቸውና የሚከተሏቸው ሥራ አጦች ብሄራቸው ሥራ አጥነታቸው ነው። የዘመኑ የወያኔ ባለሃብቶችና የሌሎች ብሄሮች ግብረአበሮቻቸውም ቢሆኑ ከድሃው ህዝብ አፍና ከልጁ ጉሮሮ ከሚነጥቁት ሃብት ሌላ የሚያውቁት ብኖርም ሆነ ቆመንለታል የሚሉት ህዝብ የላቸውም።

ይህ ስለተባለ የሃገራችን ዲሞክራቶች የብሄርን ጥያቄ ታሪካዊ ተገቢነት አምነው ለዚህ ችግር ዲሞክራሲያዊ መፍትሄ እንግበው መታገል የለባቸውም ማለት አይደለም። ለዚህ መታገልና ወያኔና መሰሎቹ በዚህ ጥያቄ እንዳይነገዱ ማከላከል ታሪካዊ ተግባራቸው ነው። ከዚህ ጋር ተያይዞ ግን የሃገራችን ዲሞክራቶች ሌላ ከባድ ሃላፊነት አለባቸው። ሥራ አጥነት፣ በኑሮ ጠርዝ ላይ መጠንጠል፣ መታረዝ፣ መናቅ መፋፊት የጋራ ብሄራዠው የሆነውን በሚለዬን የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያንን በህብረት አንቀሳቅሰው፣ የለፈፉትን ቢለፍፉ የጋራ ብሄራቸው ስግብግብነት፣ ብዝበዛ፣ ለሃገርና ለወገን ደንታ ቢስነት፣ ሃብትና ገንዘብ የሆነውንና እኛን በብሄር አጥር ከፋፍለው ለመግዛት ሌት ተቀን የሚያሴሩትን ህብረ ብሄር ግፈኞች እንዲቋቋሙ ማገዝ ታሪክ የጣለብን ሃላፊነት ነው እንላለን።